***Journal of Afroasiatic Languages, History and Culture(JAAL)*** Volume

10, Number 2, 2021

# TABLE OF CONTENTS

POLITICAL AND SOCIO-ECONOMIC SPECTACLE OF DESSIE, 1917–1991 .......... 185

*Assefa Balcha*

ORIGIN AND DEVELOPMENT OF ETHIOPIAN ORTHODOX TEWAHIDO CHURCH AND ITS LINK WITH STATE: A HISTORICAL REVIEW .......... 231

*Alemayehu Jote Tullu*

POST-1991 INTER-ETHNIC RELATIONS IN SOUTHEASTERN WOLLO: THE OROMO AND THE AFAR .......... 257

*Endris Ali Haider*

BÊTE AMHARA: THE PRE-OROMO RELIGIOUS AND POLITICAL LANDSCAPE OF WOLLO .......... 275

*Misganaw Tadesse*

FOREIGN LANGUAGES IN ETHIOPIA: A HEYDAY OF FRENCH .......... 293

*Daniel Abera*

THE PLACE OF GENDER EQUALITY, ACCOMMODATION OF DIVERSITY AND CIVILIZED SOCIETY (ENLIGHTENMENT) IN CLASSICAL ETHIOPIAN PHILOSOPHY .......... 309

*Eyasu Berento Assefa*

*Journal of Afroasiatic Languages, History and Culture*

Volume 10, Number 2, 2021

# THE PLACE OF GENDER EQUALITY, ACCOMMODATION OF DIVERSITY AND CIVILIZED SOCIETY (ENLIGHTENMENT) IN CLASSICAL ETHIOPIAN PHILOSOPHY

Eyasu Berento Assefa[1]

## Abstract

*Civilized Society/Enlightened community is a community where development and common affairs are participatory of all, entertaining better opportunities and choices for life. Such community gives proper place and recognition to the views and voices of children, women, the elderly and other historically excluded members of the community. Furthermore, such social fabric entertains diversities pertaining to religion, culture, history, and worldviews. Based on such assumptions, this study is a critical assessment on classical Ethiopian philosophy. The focus is given on participatory development related to gender equality, accommodation of diversity and enlightenment as portrayed in translated philosophical texts of the book of*

1 Mr. Eyasu Berento is a young scholar who attended his BA and MA degrees in philosophy at Addis Ababa University. He has worked as lecturer of Philosophy at Aksum University (2011-2016), worked and chaired the department of Philosophy at Mekelle University (2016-2020). He is lecturer of philosophy at Kotebe Metropolitan University (April 2020-present). As a researcher, he has participated in several national and international conferences with two peer reviewed journal articles, two book chapters, about six proceedings and other forthcoming publications.

*the wise philosophers (16th C) and original treatises of 17th C Ethiopian philosophers, Zara Yacob and Wolde Hiwot. As a philosophical reflection, the study uses qualitative research method. Accordingly, we can extract and take lessons for our contemporary aspirations of gender equality, accommodation of diversity and enlightenment from classical Ethiopian philosophy. Genuine development should entertain both material and spiritual aspects. As such, the development projects of certain society are expected to achieve healthy intergenerational communication, common aspirations for common good and desirable intercultural communication (where diversity is a challenge). Therefore, policy makers, practitioners, researchers and all concerned in Ethiopian desirable future need to consult indigenous knowledge systems besides foreign ideas, modern science and technology. This will save us from producing "educated community" who is detached from the self for the sake of embracing the identities of others.*

**Key Words**: Classical Great ideas, Diversity and Gender Equality, Enlightenment, Intergenerational – Intercultural Communications, Sustainable Development

# የሴቶች እኩልነት፣ ብዝሃነትና የሠለጠነ ማኅበረሰብ ግንባታ እሳቤዎች በዘመን ተሻጋሪ የኢትዮጵያ ፍልስፍና ውስጥ

ኢያሱ በሬንቶ

## አህጽሮተ ጥናት

*የሠለጠነ ማኅበረሰብ ሲባል ሁሉን አሳታፊና ለሰው ልጆች ሕይወት የተሻለ አማራጭ ያለበት እድገት በማረጋገጥ ላይ ያለ ማኅበረሰብ ነው። ይህም ሴቶችን፣ ህጻናትን፣ ሽማግሌዎችንና በታሪክ አጋጣሚ የተገለሉትን አካላት ያካተተ፤ የሃይማኖት፣ የባህል፣ የታሪክ፣ የአስተሳሰብ ብዝሃነትን በሆደ ሰፊነት ያቀፈ መሆን አለበት። ይህ ጥናት ሁሉን አቀፍ ማኅበረሳባዊ ስልጣኔን ለማረጋገጥ የሴቶች እኩልነት፣ ብዝሃነት[2]ና የአስተሳሰብ ልህቀት[3] ለማረጋገጥ ዘመን ተሻጋሪ የኢትዮጵያ ፍልስፍና የሚኖረው አስተዋጽኦ ላይ የተደረገ ትንታኔ ነው። ከኢትዮጵያ ፍልስፍና ገጾች በመግለጥ፣ በ16ኛው ክፍለ ዘመን የተተረጎመው "አንጋረ ፈላስፋ" ና በ17ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ ፈላስፎች መጻሕፍት (በግእዝ የተጻፉ ሐተታ ዘርዓ ያዕቆብና ወልደ ሕይወት) መጻሕፍት ላይ ትኩረት አድርጓል። ዓይነታዊ[4] የጥናት ዘዴን የተከተለ ፍልስፍናዊ ምልከታ ነው። የተደረሰውም ድምዳሜ ከዘመን ተሻጋሪ የፍልስፍና አስተሳሰቦች ውስጥ ለዘመናችን የሴቶች እኩልነት፣ ብዝሃነትና የአስተሳሰብ ልኅቀት አጀንዳዎች ዓይነተኛ ግብአት የሚሆኑ ሙግቶችንና ምክረ ሐሳቦችን ማግኘት ይቻላል የሚል ነው። የአንድ እድገት መለኪያው ቁሳዊና መንፈሳዊ እሴቶችን ሲያሟላ ነው። የተሟላ የአንድ ማኅበረሰብ ሥልጣኔ የሚረጋገጠው ደግሞ በትውልዶች መካከል (በትናንት፣ በዛሬና በነገ ትውልዶች) ጤናማ የሆነ የመንፈስ ትስስር[5] እና በባህሎች መካከል በጎ መናበብ[6] ሲፈጠር ነው። ስለዚህ ፖሊሲ አውጭዎች፣ ፖሊሲ አስፈጻሚዎች፣ የጥናትና ምርምር ባለሙያዎች እና ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት ከዘመናዊ ሳይንስ ጎን ለጎን ዘመን ተሻጋሪ አገር በቀል እውቀቶችን ቢያካትቱ ለዘመናችን ችግሮችና ለዘላቂ ልማት እቅዶች መፍትሔ የሚሆኑ ምክረ ሐሳቦችን ማግኘት ይቻላል። ከባህሉ፣ ከወላጆቹና ከአገር በቀል እውቀቱ የተነጠለ "የተማረ ማኅበረሰብ" እንዳንፈጥር በዚህ በኩል መካነ አእምሮዎች[7] ትልቅ ኃላፊነት ይጠበቅባቸዋል።*

2 Multiculturalism

3 Enlightenment

4 Qualitative

5 Intergenerational communication

6 Intercultural communication

7 Universities

**ቁልፍ ቃላት**: ብዝሃነትና የሴቶች እኩልነት፣ ዘላቂ ልማት፣ ዘመን ተሻጋሪ ሐሳቦች፣ የትውልዶች ተግባቦት፣ የአስተሳሰብ ልኅቀት

## ፩. መግቢያ

የሠለጠነ ማኅበረሰብ ግንባታ የሁሉን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ቁሳዊና መንፈሳዊ እድገትን የማረጋገጥ ሂደት ነው። ይህንን ለማረጋገጥ ደግሞ እውቀት ትልቅ ሚና አለው። ምክንያታዊ ያልሆነና ያልተማረ ማኅበረሰብን ይዞ ሁሉን አቀፍና ዘላቂ እድገትን ማምጣት አይታሰብም (ገብረሕይወት ባይከዳኝ፣ 2002)። ዘመናዊ ትምህርት መስፋፋትና ሽፋን ከፍተኛ ቢሆንም በሃገር በቀል እውቀት ላይ ጥረት ሲያደርግ አይስተዋልም። የአንድን ማኅበረሰብ ደህንነት ለማረጋገጥ ያ ማኅበረሰብ በታሪክ ሂደት ውስጥ በተለያዩ ዘመናት ያካበታቸው ቁሳዊና መንፈሳዊ እሴቶቹን መጠበቅና ከእውቀት መጋዘኑ ተጠቃሚ እንዲሆን ማስቻል አለበት። ከዚህ በተጨማሪ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ባለ ብዙ ባህል ማህበረሰብ ያላቸው አገራት የብዝሃነትን ጸጋ ሊጠቀሙበት ይገባል። ይህም ለዕውቀት፣ ለምርምር ያለንን አማራጮች በማብዛት በትውልዶች መካከል መልካም መናበብን ከመፍጠሩም በላይ በልዩነቶች መካከል መልካም ተግባቦትንና ጤናማ ማኅበራዊ መስተጋብርን ያረጋግጣል።

በአንድ አገር ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ የበዳይና ተበዳይ፣ የጨቋኝ ተጨቋኝ፣ የእኔና ሌላው ልዩነቶች መጥበብና መወገድ አለባቸው። ከነዚህ ውስጥ የጾታ እኩልነት ጥያቄ፣ የርስ በርስ ግንኙነት ያሉ የእኩልነት እና የሰላም ጥያቄዎችን ሊመለስ ይገባል። ምንም እንኳ የሌላ ባሕሎች እውቀቶች እና ፍልስፍናዎች የራሳቸው አማራጭ ያላቸው ቢሆንም በዘመናዊ ትምህርት አማካኝነት ከአገር በቀል እውቀት ጋር መቀናጀት ይኖርባቸዋል።

ይህ ጽሑፍ በየአሁኗ ኢትዮጵያ ማኅበራዊ መግባባት ላይ የብዝሃነት ጉዳይና የሴቶች እኩልነት ትኩረት ሊሰጣቸው እንደሚገባ ይሞግታል። የችግሮቹን አሳሳቢነት ግምት ውስጥ በማስገባት ዘመናዊ መንገድ ብቻውን ሙሉ በሙሉ ሊመልሰው እንደማይችል በመገንዘብ ከአገር በቀል እውቀት በተለይም ከዘመን ተሻጋሪ የኢትዮጵያ ፍልስፍና ውስጥ የሚገኙ ምክረ ሓሳቦችን፣ ሙግቶችንና አስተያየቶችን ፈልፍሎ በማውጣት ወደ አካዳሚያዊ መድረክ ያቀርባል። በዚህም በኢትዮጵያ ፍልስፍና ውስጥ ለዘመናችን የብዝሃነት፣ የሴቶች እኩልነት፣ የአስተሳሰብ ልኅቀትን ለማረጋገጥ ኢትዮጵያውያን ፈላስፎች (የፍልስፍና ተርጓሚዎች) ያደረጉትን ሙከራና ያቆዩልንን ጥበብ ከዘመናዊው ትምህርት ጋር በማዋሃድ ጉልህ ሚና ያለው እውቀት መፍጠር ይቻላል። ይህ ጽሑፍ ያተኮረባቸው ዓበይት ርእሶች የጾታ ልዩነትና እኩልነት የሚያስተናግድ፣ የባህል ልዩነትና አንድነት የሚያቅፍ፣ የሰለጠነ የውይይት ባህልና ዘላቂነቱ የተረጋገጠ ሁሉን አሳታፊ ልማት ለማምጣት የኢትዮጵያ ፍልስፍና የሚኖረውን አስተዋጽኦ ማሳየት ነው። ይህ ጽሑፍ በዋናነት በተጻፉ የፍልስፍና ድርሳናት ላይ ትኩረት ያደረገ ነው።

የጽሑፉ ዓላማ የተዘነጉ አገር በቀል እውቀቶችንና ዘመን ተሻጋሪ ፍልስፍናዎችን ከዘመናዊው ሳይንስና ፍልስፍና ጋር በማዋሃድ ከዓለም ያልተነጠለ ከባህሉና ከወላጆቹ ጋር ያልተፋታ ስልጡን ማኅበረሰብ መገንባት እንደሚገባን ማሳየት ነው። ይሕንን

ለማሳካት በጥልቅ የመጽሐፍ ይዘት ትንታኔ ላይ የተመሰረተ ዓይነተኛ የጥናት ዘዴን በመከተል የተደረገ ፍልስፍናዊ ሐተታ ነው።

ጽሑፉ ወደ ውስጣችን በመመልከት ለችግሮቻችን መፍትሄ የሚሆኑ ፍልስፍናዊ እይታዎችን ይዳስሳል። የኢትዮጵያ ፍልስፍና ምንድን ነው? የምክንያታዊ ማኅበረሰብ መገለጫዎች ምንድን ናቸው? በልዩነቶች ምክንያት የሚፈጠርን አለመግባባትና የጾታ አድልዎችን እንዴት መቅረፍ ይቻላል? ከኢትዮጵያ ፍልስፍናስ እነዚህን ጥያቄዎች መመለስ የሚችሉ ሐሳቦች ማግኘት እንችላለን? የአንድ ማኅበረሰብ ዘላቂ ሥልጣኔ መገለጫዎችስ ምንድን ናቸው? የከፍተኛ ትምህርት ሚና ምን መሆን አለበት? የሚሉ ጥያቄዎችን ለመመለስና ሌሎች እንዲመልሱትና እንዲወያዩበት የሚጋብዙ ሐሳቦችን ይዟል።

## ፪. የኢትዮጵያ ፍልስፍና

የኢትዮጵያ ፍልስፍና ምንድን ነው? የሚለውን ከማየታችን በፊት ኢትዮጵያ ምንድን ነች? ኢትዮጵያውያንስ እነማን ናቸው? የሚለውን ማየት ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያ በታሪክና በመልክአምድር የተለያየ ይዘትና ቅርጽ እየተሰጣት የቆየች ጥንታዊት አገር ናት። ከግብጽ በስተደቡብ እስከ ህንድ ውቅያኖስ የተዘረጋ መልክዓ ምድር ያላት አገር ስትሆን በህዝቡ አወቃቀር፣ ስነ ልቦናና ስብዕና የተለያዩ የታሪክ ጸሐፊዎች የተለያየ እሳቤዎችን ያስቀምጣሉ። ከነዚህም ውስጥ በታሪክ ቀደምት የሆኑ ጀግና፣ ለፍትሃዊ፣ ምክንያታዊነት ነጻ ህዝብ እንደሆኑ የሚመሰክሩ አሉ። ለምሳሌ በ16ኛው ክፍለ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ የተጓዘ አልቫሬዝ የኢትዮጵያውያንን ፍትሐዊነትንና የሥነ ህንጻ ና የሥነ ጥባብ ክህሎት ሲያደንቅ Almeida ደግሞ ኢትዮጵያውያንን "ለፍትህና ለምክንያታዊነት ዝግጁዎች፣ ብሩህ አእምሮ ያላቸው፣ በጥሩ ሥነ ምግባር ያደጉና፣ ታጋሽና ትሁት ለይቅርታ ቅርብ የሆኑና ቂም የማይዙ" ሲል ይገልጻቸዋል።[8] ሌላኛው የጥንት ዘመን ጸሐፊ Diodorus ደግሞ "በምንም የውጭ ኃይል ያልተገዙ፣ ሁሌም በነጻነት የኖሩና በፍጹም የውስጥ ሰላምና የርስ በርስ መከባበር የኖሩ ህዝቦች"[9] ይላቸዋል። ሌሎቹም እንዲሁ ዓባይን የሚቆጣጠሩ፣ አስፈሪና ጀግና ህዝቦች በማለት የኢትዮጵያውያንን ማንነት ሲገልጹ ይስተዋላል።[10]

ዋናውና መሠረታዊ ጥያቄ እነዚህ ኢትዮጵያውያን እነማን ናቸው? የሚለው ነው። የ1960ዎቹ የብሔር ጥያቄ ኢትዮጵያን እንደ ቅኝ ገዥ ከመመልከት ጀምሮ የውስጥ አድልዎና የብሔር ጭቆና አለ ወደሚሉ የተለሳለሱ አቋሞች ያስተናገደ የቅርብ ጊዜ ታሪክ

---

8 "very amenable to reason and justice … intelligent and good natured … mild, gentle, kind and so inclined to forgiveness that they readily pardon any injuries" (cited in Donald Levine, 1974, p. 10).

9 The Ethiopians "...were never brought into subjugation by a foreign prince, but always remained a free people, at perfect peace among themselves" (in Levine, p.12).

10 Ibid. 6-7

ነው። ይህም ኤርትራን እስከ መገንጠልና ብሔር ተኮር የፌደራሊዝም ሥርዓት እስከ መከተል ደርሷል። ከነዚህ እሳቤዎች ውስጥ አንዱ ኢትዮጵያን የተለያዩ ህዝቦች ስብስብ አድርጎ የሚያስበው ሙግት ነው። በዚህ ሙግት መሠረት ኢትዮጵያውያን እርስ በርሳቸው ብዙም የጋራ እሴት የሌላቸው ባንድ ላይ የተሰበሰቡ ህዝቦች ናቸው፣ ኢትዮጵያም የብሔር ብሔረሰቦች ቅርጫት ናት ወደሚለው ድምዳሜ ይደርሳል። ይህ አስተሳሰብ ግን ብዙም ተቀባይነት ያለው አይደለም። ባንድ በኩል ኢትዮጵያውያን ለዘመናት በጋራ የኖሩና ደስታና ችግርን ባንድነት የተጋፈጡ ህዝቦች ናቸው። ለዚህም ብዙ ማሳያዎች አሉ። ከነዚህ ውስጥ ሌቪን የኢትዮጵያውያንን አንድነት መካድ የሚጋሯቸውን ብዙ እሴቶች ማጣጣል እና የተሳሳተ ግንዛቤ እንደሆነ ይሞግታል። "[…] to see Ethiopia as a mosaic of distinct peoples is to overlook the many features they have in common and the existence of discernable culture areas, and to ignore the numerous relationships these groups have had with one another" (Levin, p. 21).

ይህንን ሐሳብ በርካቶች ይደግፉታል። ለምሳሌ ዲ አባዴ ስለኢትዮጵያውያን ስብጥር "የቆዳ ከለር ለዓይነት ከፈለጋችሁ በዓለም ላይ ያሉትን ሕብረ ቀለማት ሁሉ በኢትዮጵያ ውስጥ ታገኛላችሁ። የስፓኒሽ ዝርያ የሆኑ ላቲን አሜሪካኖች ያላቸውን ከመሰለው ነሐሳማ ከለር ጀምሮ የቤርቤር ጎሳዎች ወይም ኔግሮዎች ያላቸውን ልጥልጥ ኑግ መሰል ጥቁር የቆዳ ቀለም በሽ ነው።" (2009፣ ገጽ. 50-51) ካለ በኋላ እነዚህ የተለያዩ የሚመስሉ ህዝቦች እንዴት አብረው ሊኖሩ ቻሉ የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ የርስ በርስ ሰላማዊ መስተጋብራቸውን እንዲህ ይገልጸዋል፤

> ከአውሮፓ የመጣው ተጓዥ ግር የሚለው አንድ ነገር አለ። በሚያልፍበት አካባቢ የሚያየው አንድ ህዝብ መካከል ከሌላ ቦታ ተሰዶ የመጣ የሌላ አካባቢ ሰው፤ ቤተሰብ፤ እንዲያውም አንዳንዴ መንደር ሙሉ ሰው ከነባሩ ጋር ሰፍሮ ሲኖር ማየቱ ነው። ከነባሩ ነዋሪ ጋር በዘር ወይም በጎሳ የማይዛመድ ፍጹም የተለየ ብሔር ቢሆን እንኳን ተቀላቅሎ ለመኖር አንዳች ችግር አይፈጥርበትም። ለመልካም አብሮ የመኖር ዘዴ የነባሩን ነዋሪ ወይም ብሔር ሕግና ልማድ አክብሮ መስሎ መኖር ብቻ ሲጠበቅበት በበኩሉ አያት ቅድመ አያቶቹን ሳይክድ ማንነቱን ሳይረሳ ጥንታዊ ልማዱን ሳይሽር መኖር ይችላል። ለዚህም ነው በኢትዮጵያ ባንድ አካባቢ የተለያዩ ባህልና ልማድ ያላቸው ጎሳዎች በጉርብትና በሰላም ሲኖሩ ማየት የምንችለው (ዝኒከማሁ፣ ገጽ 73)።

በጉዳዩ ላይ ከሚጽፉት ጸሓፍት ውስጥ የኢትዮጵያውያን አንድነት እንደሚታየው የቀለምና የኑሮ ዘዴ ስብጥር የጎላ ሳይሆን እንዲያውም ሁሉም አንድ ዓይነት ህዝቦች ናቸው። በመካከላቸው የባህልና የነገድ ልዩነት ማግኘት ከባድ እንደሆነ የሚገልጹ ብዙዎች ናቸው። ሌቪን ከነዚህ ወገኖች የሚመደብ ነው። ተከለጻድቅ መኩሪያ እንዲህ ይገልጸዋል፤

> … የጥንት ጽሐፊዎች ግብጾችም፣ እስራኤሎችም ግሪኮችም ግማሾቹ የኩሽ አገር የቀሩት ኢትዮጵያ እያሉ ሲጠሩን አሁን ባለንበት የፖለቲካና ያገር ክፍል የምንገኘውን ኢትዮጵያኖች ብቻ አይደለም[።] ነገር ግን ከዛሬው ቱኒዚና ማሮክ ከሊብያና ግብጽ ከፍልስጥኤም ወደ ደቡብ በኤርትራ ባህር ግራና ቀኝ እስከ ህንድ ውቅያኖስ ጠረፍ ድረስ ያለውን የዛሬውን የዓረብንም የሱዳንንም በመካከል የሚገኘውን ያሁኑን የኛንም አገር አንዳንድ ጊዜ እየለዩ ብዙ ጊዜ እየደባለቁ ነው።
>
> ይህም እንደ ሙሉ ስህተት እንዳይቆጠር በዙሪያችን ከሚገኙት ከነዚህ ህዝቦች ጋር ዘራችን ልማዳችን ቋንቋችን ከሥር ከመሠረቱ እየተገናኘ ተደባልቆ በመኖሩ ነው፤ ደግሞም ረኃብ በተነሳ ጊዜ አንደኛው ነገድ ተሰዶ ወደ አንደኛው ነገድ አገር ሄዶ ይደባለቃል። (፲፱፻፵፮, ገጽ. ፲)

በኢትዮጵያ ፍልስፍና ዙሪያ ከፍተኛ ጥናት ያደረገና ከግማሽ ደርዘን በላይ መጻሕፍትን የጻፈ ክላውድ ሳምነርም ይህንን ሐሳብ ይደግፋል።

> As there has been so much racial intermixing, racial identifications are limited use in Ethiopia. Periodic migrations of Caucasoid peoples from across the Red Sea and the Negroid peoples from the West have produced a population that predominantly manifests a blend of the two physical types. … The terms Amhara, Oromo, and Tigré refer to linguistic and to some extent cultural groups, rather than to races or tribes (1985, p. 2).

እነዚህ ሐሳቦች ሰብሰብ አድርገን ስንመረምራቸው ያሁኑ ኢትዮጵያውያን ባንድም በሌላም መንገድ አብረው የኖሩ፣ የተዋሃዱና የተዋለዱ ህዝቦች እንደሆኑ መደምደም ይቻላል። አሁን ባለው ማኅበረ ፖለቲካዊ መዋቅር ውስጥ የሚተዳደሩትንም ሆነ በተለያየ መንገድ ውጭ እየኖሩ ራሳቸውን እንደኢትዮጵያውያን የሚቆጥሩ፣ በህጋዊና በስነ ልቦናዊ ምክንያት ኢትዮጵያውያን ነን የሚሉትን ነው ኢትዮጵያውያን የምንላቸው።

የኢትዮጵያ ፍልስፍና ስንልም የነዚሁ ህዝቦች በጽሑፍና በቃል ሲተላለፍ የመጣ የአስተሳሰብ ከፍታ ነው። ሐተታ ተፈጥሮን ለመመርመር፣ ማህበራዊ መስተጋብርን ለመበየን፣ ሕይወትን ለመተርጎም፣ ደስታና ሐዘንን ለመግለጽ፣ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ችግሮችን ለመፍታት ሰዎች ከሰዎች ጋር ባላቸው ግንኙነትና የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ጋር በሚያደርገው ቁርኝት በዘመን ሂደት ውስጥ የሚኀለብቱ አገር በቀል እውቀቶች ውስጥ ፍልስፍናን ማግኘት ይቻላል። ከዚህም በተጨማሪ በግለሰቦች የግል ጥረትና ምርምር፣ ተመስጦ የሚፈልቅ ያስተሳሰብ ልሕቀትን የኢትዮጵያ ፍልስፍና እንለዋለን። ከዚህም በተጨማሪ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት የተተረጎመና ለኢትዮጵያ ባኅል እንዲመች ተደርጎ

የተዋሐደ የውጭ ፍልስፍና በዘመን ሂደት ውስጥ ኢትዮጵያዊነትን ተላብሶ ይገኛል። ይኸም ከኢትዮጵያ ፍልስፍና የሚመደብ ይሆናል።

ከነዚህም ውስጥ የጋዳ ፖለቲካዊ ሥርዓት፣ የጋዳ የተፈጥሮ ጥበቃ ሥርዓት፣ የሰለሞናዊ ፖለቲካ ሥርዓት በኢትዮጵያ፣ የየተተረጎሙ የፍልስፍና መጻሕፍት፣ በዘርዓ ያዕቆብና ወልደ ሕይወት የተጻፉ የፍልስፍና ሐተታዎች፣ ሌሎችም የኢትዮጵያ ፍልስፍና ቅርሶች ናቸው። ምንም እንኳ በባህልና በቦታ ርቀት ወደሌላው ባይዳረሱም በየትኛውም የኢትዮጵያ አካባቢ የፈለቀና በማንኛውም ቦታ ቢተገበር የወገንተኝነትና የባሕል ተቃርኖ እስካላመጣ ድረስ የኢትዮጵያ ፍልስፍና ነው ልንለው እንችላለን። ዘመን ተሻጋሪ የኢትዮጵያ ፍልስፍና የተሰኙትም በጊዜና በቦታ የማይገደቡ በኢትዮጵያውያን የሚተገበሩና፣ የተነገሩና የተጻፉ የፍልስፍና ሐሳቦችን የሚገልጽ ነው።

ከነዚህ የፍልስፍና ቅርሶች ውስጥ ነው ለአስተሳሰብ ልኅቀት፣ ለሴቶች እኩልነት፣ ለብዝኃነትና ለዘላቂ ልማት እሳቤዎች የሚሆኑ ሙግቶችንና ምክረ ሐሳቦችን ማግኘት የምንችለው። ለምሳሌ የፍልስፍናን ሚና ከሚያትቱት መካከል አባ ሚካኤል የተባሉ የአንጋረ ፈላስፋ ደራሲ የተለያዩ ፈላስፎችን አባባሎች በሰበሰቡበትና በተነተኑበት መጽሐፍ የሚከተለውን ይላሉ፤

> የፈላስፎች ፍልስፍናና የአዋቂዎች ዕውቀት ከብር፣ ከወርቅ፣ ከአልማዝ እርሷ ትበልጣለች ትመረጣለችም። እንዲሁም ልዩ ልዩ ጣዕምና መዓዛ ካላቸው ከአታክልት አበባዎች መዓዛ የርሷ መዓዛነት ይበልጣል። [...] አንደበትህን በጥበብ፥ በዕውቀት፥ በቅንነት፥ በትዕግስት፥ በማስተዋል ጨው ታጣፍጠዋለች። ጠባይህን ያማረ የተወደደ፥ አነጋገርህን በሚሰሙት ሰዎች ዘንድ ተደማጭ ታደርገዋለች። ሥራህን ሁሉ ታከናውንልሃለች። (፲፱፻፶፫፣ ገጽ ፯)

እነዚህ ቃላት የፍልስፍናን ሚና አጉልተው ያሳያሉ። ለሰላም፣ ለአብሮነትና አስተሳሰብ ልህቀት ፍልስፍና ጉልህ ሚና አለው። የጸባይ ቀናነትን፣ የአስተሳሰብ ቀናነትንና የስብዕና ጽርየትን[11] ታጎናጽፋለች። አሁን ያለው የብሔር ተኮር ፖለቲካ ዲስኩር የተለያየ አመላካከቶችን ሲያስተናግድ ይታያል። በኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያዊነት ዙርያ የሚነሱት አለመግባባቶች ከሐሳብ ግጭትም አልፈው ለመሰደድ፣ መፈናቀል፣ ለበርካቶች ሞት መንስኤ ሲሆኑ ይስተዋላል። በዚህም የተግባቦት፣ የአብሮነት እና የእኩልነት ችግር በዘላቂነት ለመፍታት የተግባቦት ወዘናው ለዛ ያለው ምክንያታዊ ማኅበረሰብ ለመገንባት ፍልስፍና የአንበሳውን ድርሻ ይይዛል።

## ፫. ምክንያታዊ ማኅበረሰብ

11 perfection of personality

ምክንያታዊ ማኅበረሰብ ሲባል በአስተሳሰብ ልኅቀት የጠነከረና በስሜት የማይነዳ ማኅበረሰብ ነው። የመመራመር ባህሉ ጠንካራ የሆነ በሥማ በለውና ዘፈቀዳዊ እምነት የማይመራ ማኅበረሰብ ነው። የሰው ልጅን መለኮታዊ ባህርይ ግምት ውስጥ በማስገባት ቀደምት የኢትዮጵያ ፈላስፎች ሳይመረምሩ ማመንን እንደ ኃጢአት ወስደውታል። በኢትዮጵያ ፍልስፍና ውስጥ የመመራመርንና የምክንያታዊ ማኅበረሰብን ግንባታ ከሚመኙና ለዚያም ከሚሞግቱት ፈላስፎች ጥቂት እሳቤዎችን እንውሰድ።

ዘርዓ ያዕቆብም “ሰዎች ሁሉ ለባውያን ናቸውና” (2007፣ ገጽ 15) ሲለን ለባዊነት ምክንያታዊነትና ተመራማሪነት የሰው ልጆች መለኮታዊ ጸጋ የሆነ ጥንተ ተፈጥሮ እንደሆነ ሲጠይቅ ነው። ለዘርዓ ያዕቆብ የአንድ ነገር እውነታኛነት የሚረጋገጠው በአማኞቹ ብዛት ሳይሆን ከልቡና ጋር ባለው ስምምነት ይወሰናል። እንዲያውም ልክ እንደ ጀርመናዊው ፈላስፋ ኢማኑኤል ካንት እንደሚለው የአንድ ነገር እውነተኛነት ለማረጋጋጥ የሰዎች ምስክርነት ላይ ብቻ መንጠልጠል እንደሌለብን ይነግረናል። “ሕያው ፈጣሪያችን በእውቀትና በተግባር ኑሯችንን እናሳምረው ዘንድ ይፈቅዳል። ስለዚህ ልብና ችሎታን ሰጥቶናልና።” (ዝኒከማሁ ገጽ 19-20) የራሱን ልምድ ሲነግረን “ከዳዊት መዝሙር ውስጥ ከኅሊናዬ ጋር የማይስማማ ባገኝ እኔ እተረጉመዋለሁ” (22) ይለናል።

ወልደ ሕይወትም ሳይመረምሩ ማመንን በእጅጉ የሚያወግዝ ፈላስፋ ነው። ከመምህሩ የተቀበለውን አደራ በማስቀጠል ስለ መመራመር አስፈላጊነትና የሥልጡን ማኅበረሰብ ግንባታውን ተግባራዊ ለማድረግ መመራመርን እና ምክንያታዊነትን በህዝቡ ዘንድ እንዲሰርጽ በአጽንኦት አስተምሯል።

> ወንድሜ ሆይ አዋቂ አድርጎ ወደ ፈጠረህ ፍጹም ወደ ሆነው ወደዚህ ኅላዌ ኅሊናህን ከፍ ከፍ አድርግ። በዓይነ ልቡናህም ወደ እርሱ ተመልከት። ፈጣሪህ የሚያሳይህን የአእምሮ ብርሃንም አስተውል።... አንተስ ሰዎች ያስተማሩህን እውነትን ከሃሰት ትለይ ዘንድ ሳትመረምር ፈጽመህ አትመን፤ ሰዎች ሊዋሹህ ይችላሉና። እውነትን ወይም ሐሰትን ቢያስተምሩህ አንተ አታውቅምና። እንዲሁም በመጻሕፍት የተጻፈውን ፈጽመህ አትመን። መርምረህ እውነተኞች ሆነው ካላገኘሃቸው በቀር። መጻሕፍትንም ሐሰትን ይጽፉ ዘንድ የሚችሉ ሰዎች ጽፈዋቸዋልና (ዝኒከማሁ፣ ገጽ 42)።

በሚያስደንቅ ሁኔታ ምርምርን ወደ ጥበብ የምንገባበት በር ሲያደርጋት ልቡናችን [ኅሊናችን] ደግሞ ይህንን በር የምንከፍትባት ቁልፍ ናት። እንዲያውም ቀድሞ በችኮላ ከማመን ይልቅ አለማመን እንደሚሻል፣ ካለማመን ወደ ማመን፣ ከመጠራጠር ወደ መመራመርና ወደ እርግጠኝነት እንደምንደርስ ይከራከራል። “ለማመን እንጅ ላለማመን ምክንያት አያስፈልግምና።” ካለ በኋላ የሰው ልጅ “መልካሙን ከክፉ፣ እውነቱን ከሐሰት እንድ[ን]ለይ የልቡናን ብርሃን ሰጥቶናል።” ይላል (ዝኒከማሁ፣ ገጽ 48)። ከዚህ የመመራመር ተፈጥሯዊ ጸጋ የሚመጣ ተጠያቂነትም አለ። ለባዊት ነፍስና ተመራማሪ አእምሮ ተሰጥቶን ባንመረምር ኃጢአት እንደሰራን ይፈረድብናል። “ሁሉን መመርመር መልካም ጥበብ ነውና። ነባቢት ነፍስንና ይህን የሚመረምር ልቡናን ለሰጠን ለፈጣሪያችን

እናመሰግነዋለን። ሳይመረምሩ ማመን ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። ከለባዊት ፍጥረት[12] ባህርይ ጋርም አይስማማም" (ዝኒከማሁ፣ ገጽ 49-50)።

ከሌሎች ጥንት የኢትዮጵያ ፈላስፎች ውስጥ በ5ኛው ክፍለ ዘመን ወደ ግዕዝ እንደተተረጎመ የሚነገርለት የእስክንድስ ሕይወትና መርሆዎቹ በመባል የሚታወቅ መጽሐፍ አለ። ታሪኩንና ሐሳቦቹ ባንድ ላይ የያዘ መጽሐፍ ሲሆን ለእስክንድስ አንድ ነገር እውነት ነው ለመባል መጀመሪያ በመረጃ የተደገፈ ማረጋገጫ ሊኖረው እንደሚገባ ነው። (እስክንድስ፣ በሳምነር 1985፣ ገጽ 169)

በአንጋረ ፈላስፋ መጽሐፍ ውስጥም የአያሌ ፈላስፎች ሐሳብ በሥነ ምግባር፣ በማኅበራዊ ሕይወት፣ በሰው ልጆች ባሕርይ፣ በነፍስ ተፈጥሮ፣ በሥጋ ባህርያት ወዘተ በርካታ ሐሳቦችን ያሰባሰበ ሲሆን ስለ ሰው ልጆች መመራመር አስፈላጊነት በሰፊው ይገልጻል። ምክንያታዊ ማኅበረሰብ ዋና መገለጫው የቀረበለትን እውነትና መረጃ መመርመርና ከምርምር በኋላ ማመን ነው። ከዚህ ባሻገር በማኅበራዊ መስተጋብር ውስጥ ያሉ የአስተሳሰብ ዝንፈቶችንና ተቃርኖዎችን እንዲያርቅ፣ ልዩነቶችን እንዲያስተናግድ፣ በውይይትና በክርክር እንዲያምን ይፈለጋል። "ተፈራራጅዎችና ተከራካሪዎች ያሏትን አገር ስሕተት አያገኛትም።" (አንጋረ ፈላስፋ፣ ፲፱፻፶፫፣ ገጽ ፻፴፩-፻፴፪)

ምክንያታዊ ማኅበረሰብ በውስጡ ያሉ የባህል፣ የሃይማኖት፣ የኢኮኖሚ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ተቃርኖዎችን በመፍታት ከአስተሳሰብ ዝንፈትና ከተግባቦት ኩልሸት ራሱን የሚታደግ ነው። በሰብዓዊነት እሳቤ የጎለበተ፣ ነገሮችን በሰለጠነ መንገድ የመረዳትና የመተርጎም ባህሉ የጠነከረ ማኅበረሰብ ነው። በልዩነቶች መካከል ያሉን የጋራ እሴቶች ፈልፍሎ በማውጣት የርስ በርስ ሰንሰለትን መፍጠር የሚችል በልሂቃኑ ይሁንታ፣ በፈላስፎቹ ሙግት፣ በሳይንስ ውጤት፣ በታላላቆች ምክር፣ በሃይማኖት ህጎች እየተመራ ከነባራዊው መስተጋብር ጋር እየተስማማ መሄድ የሚችል ማኅበረሰብ ነው።

ይህ ሲሆን አንድ የሰለጠነ ማህበረሰብ ሁለት አበይት ጸጋዎችን ይጎናጸፋል። ባንድ በኩል ከዘመን አይሽሬ የአባትናቶቹ መንፈስ ጋር በመተሳሰር ጤናማ የትውልዶች ተግባቦት ይኖረዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ልዩነቶችን በሆደ ሰፊነት አቅፎ በመያዝ ብዝሃነትን በማስተናገድ በባህሎችና በተፈጥሮአዊ ልዩነቶች መካከል ጤናማ መናበብ በመፍጠር የተሻለ ነገን ያረጋግጣል። ሰው የማኅበራዊ መስተጋብሩና የባህላዊ ከዋኔዎቹ ውጤት ነውና ከትናንት የተነጠለ ወይም ከሌሎች የተገለለ ማኅበራዊ ሕይወት የተሟላ አይሆንም (ፈቃደ አዘዘ፣ 2004)። እንደዚህ ዓይነቱ ማኅበረሰብ የመጨረሻ ግቡ የሰው ልጆች ደህንነት የተረጋገጠበትና የግብረገብ ፍጽምና ላይ የተቆናጠጠ (ካንት) የግለሰቦች ሙብት ዋስትና

12 ለባዊት ፍጥረት Rational Creature የሚለውን ይመለከታል። የሰው ልጅ ምክንያታዊ እንስሳ መሆኑ ከጥንት ፈላስፎች ጀምሮ ሲነገር የቆየ ጉዳይ ነው። የሰው ምግባር ሁሉ ከዚህ የተፈጥሮ ማንነቱ ጋር ስምሙ መሆን እንዳለበት ከጥንት የግሪክ ፈላስፎች ጀምሮ የዲበ አካልና የግብረገብ ፍልስፍናዎች ማዕከላዊ ርእስ ነው። ለምሳሌ ሶቅራጠስ (ፕሌቶ)፣ አሪስቶትል፣ ሲሴሮ፣ ኢማኑኤል ካንት ወዘተ ሲያስተጋቡት የኖሩት ጉዳይ ነው። የወልደ ሕይወት ፍልስፍናም "Man is Rational Animal" "ሰው ለባዊ (ምክንያታዊ) እንስሳ ነው" ከሚሉት ጋር ይስማማል።

ያገኘበት ማኅበረሰብ ነው። የዚህ ህብረት ወይም ምክንያታዊ ማኅበሰብ ፍጽምና የሚረጋገጠው ደግሞ ፍትሐዊ መንግስትን በመመስረት ይሆናል።

በሰው ልጆች ህብረት መካከል ጎልተው ከሚታዩ ልዩነቶች መካከል የባህል ብዝሃነትና የጾታ ልዩነት ይገኙበታል። በሰው ልጆች ታሪክ ሰው ሰራሽ ማኅበራዊ ጭቆና ከሚደርስባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል ሴቶች ሲሆኑ በአሁኑ ዓለም ህዝብ ዘንድ ወደ ግጭት የሚያመሩ ልዩነቶች የሚከሰቱት በባህል ልዩነቶችና ቅራኔዎች በሚፈጠሩ ስስ ብልቶች ነው (ሃንቲንግተን፣ 1993)።

ከዚህ በመቀጠል የሴቶች እኩልነትና ብዝሃነት በኢትዮጵያ ፍልስፍና እንዴት ይታያሉ የሚለውን በተናጠል እናያለን።

## ፬. የሴቶች እኩልነት

የሴቶች ጭቆና ተፈጥሯዊ የሚመስሉ መለያዎችን በመጠቀም ወንዶች የፈጠሩት የማኅበረ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እሳቤዎች የወለዱት ዓለማቀፍ ችግር ነው። በመላው ዓለም የሚከሰት የጋራ ችግር ሲሆን ሴቶችን ያገለለ ፖለቲካ ኢኮኖሚ በመፍጠር የራሱ የሆነ አሉታዊ ጫና ፈጥሯል። የችግሩ መንሥኤና መሠረቱ ሥር የሰደደ ቢሆንም በዓለም ህዝቦች መካከል ችግሩ መፈታት እንዳለበት ግን የማይስማማ የለም። በዘርዓ ያዕቆብና በወልደ ሕይወት ፍልስፍና ውስጥ በሰፊው የምናገኘው የሴቶችን እኩልነት ነው። በ17ኛው ክፍለ ዘመን ይታሰባል ተብሎ ለመገመት ከባድ የሆኑ ጾታዊ እሳቤዎች በነዚህ ፈላስፎች ዘመን ተሻጋሪ ስራዎች ውስጥ በሚያስደንቅ ሁኔታ ይገኛሉ። በምሳሌ በማስደገፍ እንመልከት።

ዘርዓ ያዕቆብ ስለ ራሱ ሕይወት ከሚነግረን ታሪኩ ውስጥ እንዴት ጋብቻ እንደመሠረተ የሚያትትበት ይገኛል።

> ስሟ ኂሩት የምትባል የጌታዬ ቤተሰብ የሆነች ሴት ልጅ ነበረች። እርሷ መልካም ምግባር ያላት አስተዋይና ትዕግስተኛ እንጅ ውብ አልነበረችም። ለጌታ ሃብቱም “ይህች ልጅ ሚስት ትሆነኝ ዘንድ ስጠኝ” አልሁት። ጌታ ሃብቱም እሺ በጄ ብሎ “ከዛሬ ዠምሮ የአንተ አገልጋይ እንጂ የኔ አገልጋይ አትሆንም” አለኝ። እኔም “ሚስቴ ትሆናለች እንጅ አገልጋዬ አትሆንም። ባልና ሚስት በጋብቻ እኩል ናቸውና። ጌታና አገልጋይ ልንላቸው አይገባም። አንድ ሥጋና አንድ የኑሮ ስልት ያላቸው ናቸውና፤” አልሁት። ጌታ ሀብቱም “አንተስ የእግዚአብሔር ሰው ነህ፤ እንደወደድህ አድርግ” አለኝ። ያችንም ልጅ ጠራናት። እኔም “ሚስቴ ትሆኘ ዘንድ ትወጃለሽን?” አልኋት። እሷም “እንደጌታዬ ፈቃድ ነው” አለችኝ። ጌታ ሀብቱም “እኔስ እፈቅዳለሁ” አላት። እርሷም “ለእኔ መልካም ነው፤ ከአንተ የሚሻል ለእኔ የት አገኛለሁ” አለችኝ። ለጌታ ሃብቱም “አባታችን ሆይ መርቀን” አልነው። እርሱም “እግዚአብሔር ይባርካችሁ፣ ይጠብቃችሁ፣ ለረዥም ዘመን ጤናና ፍቅር ይስጣችሁ። ከዚህ ዓለም ገንዘብ ጋር ልጆችን ይስጣችሁ። ክፉ ነገርንም ከእናንተ ያርቅ” አለ። እኛም “አሜን አሜን” አልን። (ገጽ 27-28)

ዘርዓ ያዕቆብ በማስከተል ሁለቱ በፍቅርና በመተሳሰብ በሰላም ልጅ ወልደው፣ ሃብት ንብረት አፍርተው ለረጅም ዘመናት እንደኖሩ ያትታል።

ከዚህ ታሪክ ውስጥ ለዘመናችን የሴቶች እኩልነት፣ የጋብቻ ሥርዓት፣ የባልና የሚስት ውሳኔ እንዲሁም የትዳር ኑሮን ፍልስፍና በሰፊው እንማራለን። ሲጀምር መልክና ውበት የትዳር መስፈርት እንዳልሆኑና ሁሉም ሴቶች ለጋብቻ በሚፈለጉበት ጊዜ ጠባያቸውና አስተዳደጋቸው ቅድሚያ እንደሚሰጠው ይነግረናል። ከዚህ በመቀጠል ጌታው ልጅቷን "ከፈለግሃት ውሰድና አገልጋይ አድርጋት" ሲለው ዘርዓ ያዕቆብ አገልጋይ ገረድ ሳይሆን የተቀደሰች ባለቤቱ እንድትሆን በዚህም ሁለቱ እኩል እንደሆኑ ሞገተ። ጌታ ሃብቱም ባህሉንና ማኅበራዊውን መስተጋብር የሚቃወም ያልተለመደ ነገር በሰማ ጊዜ በአድሃሪነት መንፈስ አልተከራከረም። ይልቁን ለዘርዓ ያዕቆብ "አንተስ የእግዚአብሔር ሰው ነህ" ሲል አሞገሰው እንጅ። ከዚህም በመቀጠል ልጅቷ ተፈቅዳልኛለች ብሎ ወደ ቤቱ አልወሰደም። የልጅቷም መልካም ፈቃድ ያስፈልግ ነበርና ተጠየቀች፣ ውሳኔዋን በግልጽና በደስታ አስታወቀች። የልጅቷ ግልጽነት ከዘመኑ ልጃገረዶች ባህል የተለየ ይመስላል። የልጅቷም ፈቃድ በተረጋገጠ ጊዜ ብዙ ወጭ የሚያስወጣ የይስሙላ ሰርግ ከማረግ ይልቅ ባህሉ በሚፈቅደው ምርቃትን ተቀበሉ። በመፈቃቀርና በመተጋገዝ የራሳቸውን ኃላፊነት እየተወጡ መኖር ጀመሩ። "እሷም በመዓልትና በሌሊት ትፈትላለች። እኔም እጽፍ ነበር። " ይኸም ብቻ አይደለም ለአራት ዓመታት ልጅ ባይወልዱም ይህ ጋብቻቸውን አላናጋውም። በፍቅር ኖሩ እንጅ (ዝኒከማሁ፣ ገጽ 28) ።

ዘርዓ ያዕቆብ የሞገተው ስለ ሴቶች እኩልነት ብቻ አይደለም። በዘመኑ ስለነበሩት ትዳር ነክ ጉዳዮችም እንጅ። ከነበረው ተጽዕኖ አንጻር ካየነውም ጌታው ሀብቱንና ኂሩትንም የሱን አስተሳሰብ እንዲቀበሉ አድርጓል። ከዚህ በተጨማሪ በርካታ ተማሪዎች ነበሩት። በርግጥ ሌሎቹ በወቅቱ ሐሳባቸውን ወደ ሕዝብ ይዘው ለመውጣት ፈርተው ቀርተዋል። ከተማሪዎቹ ውስጥ እርሱን የተከተለና የዘርዓ ያዕቆብን ሐሳብ በደንብ በመደገፍ ተግባራዊ ፍልስፍናን[13] እንዳስፋፋ ተጽፎ ያገኘነው ግን ወልደ ሕይወት የተሰኘ

13 "ተግባራዊ ፍልስፍና (practical philosophy or Applied Ethics) የሚባለው በፍልስፍናዊ እሳቤ፣ በምክንያታዊ ሙግት የተለያዩ ማህበረሰባዊ ክዋኔዎችን፣ ግላዊ ጠባዮችን፣ ሐተታ ተፈጥሮን፣ ተግዳሮቶችን እና ተግባቦቶችን መቃኘት ነው። "Practical Philosophy is a discipline that uses philosophical methods and insights to explore how people can lead wiser, more reflective lives. It is also the name for the activity that helps people lead such lives. Its topics include the nature and pursuit of wisdom relating to:- the good life, reason and the emotions, decision-making and the meaning of life." (Tim LeBon, 2007) ፍልስፍና ስለማይጨበጡና ስለማይዳሰሱ ሐሳባዊ ስለሆኑ ነገሮች ብቻ የሚደረግ ዲስኩር አይደለም። ይልቁን ተግባሪ አካልን አገናዛቢና አሳቢ ህሊናን፣ አፍቃሪ ልብን፣ ባጠቃላይ ስብዕናን የማነጽ ሚናን ይጫወታል። ብዙ ፈላስፎች እንደሚስማሙበት የፍልስፍና ሚና ማሳ ወርዶ በቆሎ ማብቀል፣ ጓዳ ገብቶ እንጀራ ማብሰል፣ ሆስፒታል ገብቶ ህሙም መፈወስ፣ በሸንጎ ፍርድ መስጠት አይደለም። ይልቁን ይህንን ማድረግ የሚችለውን ህሊና ማረቅ፣ ተግባሩን በአግባቡ እንዲወጣ ማስተካከል ነው። ከዚህ አንጻር ለተለያዩ አካላት ስለ ቀን ተቀን እንቅስቃሴዎች በኀነት ምክረ ሃሳብ፣ ስለ ችግሮች መፍትሄ

ደቀ መዝሙሩን ብቻ ነው። በሴቶች እኩልነት ዙሪያ የጻፋቸውም ሙግቶች የዘርዓ ያዕቆብን ሐሳብ የሚያጠናክሩ ናቸው።

> በመዋቲው ሥጋችን ውስጥ ይህንን የመፈላለግ ስሜት የፈጠረልንን አምላካችንን እናመሰግነዋለን። ... ከዝሙት፣ ተፈጥሮህ ባልሆነ መንገድ ዘርህን ከማፍሰስ፣ ምውት ከሆነውም ምንኩስና ራቅ። ፈጣሪህን በማመስገንና በማድነቅ ወደ ሚስትህ ቅረብ። ወደ እርሷ በተጠጋህ ጊዜም የሩካቤውን ጣእም ለብቻህ አትሻ። ለሚስትህም የጣዕሙን ስሜት እንዲኖራት አድርግ እንጂ። እግዚአብሔር የሰጣትን ድርሻዋን አታሳጣት። በችኮላ አታድርግ። እርሷ እስክትስማማበት ድረስ ወደ ኋላ ቀርታ ጣዕሙ እንዳይጎድልባት ስለ እርሷ ጥቂት ቆይ። ይህንን ፍቅር ካላደረግህላት አዝና ትለይሃለች። ያንተም ጋብቻ ለእግዚአብሔር በረከት የተገባ አይሆንም።... ነገር ግን እንዳትደክም ሩካቤን ያለ መጠን አታብዛ (ዝኒከማሁ፣ ገጽ 85)።

የጋብቻን ክብር በአጽንኦት ከሞገተ በኋላ ፍችን ለማስቀረት ለሁለቱም ምክር ይለግሳል። ይህ የተጠቀሰው ሐሳብ እንዲያውም ሴት እንኳንም የቁሳዊና ሌሎች ነገሮችና የሩካቤን ጣእምና እርካታም እኩል ትካፈል ዘንድ መብት እንዳላት ይከራከራል። ፍችንና ዝሙትን የሚያወግዙ ምሳሌዎችን እየጠቀሰ ካብራራ በኋላ "ሽካራ በሆነው ጠባያችሁና ስውር በሆነው ነውራችሁ እርስ በርሳችሁ የምትቻቻሉ ሁኑ። በዓለም ሁሉ ነውር የሌለው ወንድና ነውር የሌላት ሴት አይገኝምና" (ዝኒከማሁ፣ ገጽ 88) በማለት ያሳስባል።

ከአንጋረ ፈላስፋም የሴቶችን እኩልነት የሚያትቱ ሐሳቦችን ማግኘት እንችላለን። "ፈላስፋ እንዲህ አለ፥ ሚስትህን እንደ አንዱ አካልህ አድርገህ እያት፥ ባልና ሚስት አንድ አካል፥ አንድ አምሳል ናቸውና። [...] ሚስቱን የሚያከብር ሰው እንደ መላእክት ነው" (፲፱፻፶፫፣ ገጽ ፷፮)። ስለ ሚስት ጥንቃቄም "በማይገባና በሚያስቀና ነገር ሚስትህን አታስቀናት (አትቅናባትም)" በማለት ለትዳርና ለሚስትና ባል ሥነ ልቦና ጥንቃቄ እንዲደረግ ይመክራል (ገጽ ፸፬)። ሚስት እናት ስለሆነችና እንደ እናት መከበር እንዳለባት ሲያትትም "ልጄ! ሚስትህን እንደ ራስህ አድርገህ ውደዳት። እርሷ የልጆችህ መገኛ ናትና አንተም እንደ እርሷ ካለች እናት መገኘትህን አስታውስ።" (ገጽ ፺፫)

ከነዚህና መሰል የኢትዮጵያ ፍልስፍና የሴቶችን እኩልነት የሚያበረታቱ ሃሳቦችን ማግኘት ቀላል ነው። ከላይ እንዳየነው በሴትና በወንድ መካከል መበላለጥ እንደሌለ እንዲያውም በሃይማኖት እንደሚሰበከው ሁለቱ እኩልና አንድ አካል አንድ አምሳል እንደሆኑ ፈላስፎቹ ይሞግታሉ። ከዚህም ባሻገር የሴቶችና የወንዶች ግንኙነት ጎልቶ የሚታይበት ትዳር የተከበረ እንዲሆን ወደ ፍች የሚወስዱ ነገሮችን ቀድመው መከላከል እንዳለባቸው ያሳያል።

---

መላምት፣ ስለ ግንኙነቶች ቀናነት ወዘተ የሚያትት የፍልስፍና ክፍል ተግባራዊ ፍልስፍና ይባላል። የወልደ ሕይወት ፍልስፍና አብዝሃኛው ክፍሉ ወደ ተግባራዊ ፍልስፍና የሚመደብ ነው።" (ኢያሱ በሬንቶ፣ 2009፣ ገጽ 14 የግርጌ ማስታወሻ)

## ፩. ብዝሃነት

"ብዝሃነት" የሃይማኖት፣ የባህል፣ የአስተሳሰብ ልዩነቶችን ያቀፈ የጋራ ዓላማና እሴት ያላቸው ሰዎች ስብስብ ነው። እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገሮች ባለ ብዝሃ ብሄር አገሮች ናቸው። ብዝሃነትን የማያስተናግድ ማኅበረሰብ የውስጥ ሰላምም ሆነ እድገት አይኖረውም። ብዝሃነትን ለማስተናገድ የአስተሳሰብና የምክንያታዊነት ባህል እንደሚያስፈልግ ከላይ ተጠቅሷል። በዋናነት የዘርዓ ያዕቆብና የወልደ ሕይወት ፍልስፍናዎች ብዝሃነትን የሚያስተናግድ ተመራማሪና ስልጡን ማኅበረሰብ ለመገንባት ሙከራ አድርገዋል።

በዚህ በኩል ወልደ ሕይወት በአጽንኦት የሚሞግተው ሁሉም የመሰለውን እምነትና ባህል ቢይዝም ይህንን መብቱን ግን ልናከብርለት እንደሚገባ ነው። ምክንያቱም ከሰዎች ሁሉ ጋር በሰላም ለመኖር ብዝሃነትን ማስተናገድ ግድ ስለሚል ነው። ከዚህም ባሻገር ሁሉም በታሪክና በቦታ አውድ አጋጣሚ የተለያየ እምነትና ባህል ይኑራቸው እንጅ ሁሉም እኩል የሆኑ የሰው ልጆች ናቸውና። "ደጎችም ቢሆኑ ክፉዎች፣ ክርስቲያንም ቢሆኑ እስላም፣ አይሁድም ቢሆኑ አረማውያን ሁሉም ከእኛ ጋር እኩል ናቸው (ገጽ 64)። [...] ሰዎች ሁሉ በተፈጥሯቸው እኩል፣ ሁላቸውም የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆኑ ልናውቅና ልናስተውል ይገባናል። እኛ ግን ሰዎችን ስለ ሃይማኖት ብንጠላቸው እንበድላለን። ለሁሉም ለእያንዳንዱም እውነት የመሰለውን ያምን ዘንድ ሥልጣን ያለው ነውና" (ገጽ 66)።

ለሰላማዊ አብሮነት ሲባል የሰዎችን ባህል ማክበርና እንደነሱ መኖር እንደሚገባ ይሞግታል። "ወንድሜ ሆይ አንተ ግን መልካም የሆኑ ዘመናትን ታይ ዘንድ ብትወድ በፍቅርና በሰላም ከሰው ሁሉ ጋር ተስማማ። በሃገር ሳለህ እንደ ሃገር ባህል ኑር። ወደ ሌላው ሃገር ብትሄድ ግን እንደነርሱ ሆነህ ኑር። ... ከዚያች ሃገር ሰዎች ጋር አብረህ ኑር። ለሁላቸውም እንደ ጠባያቸውና ባህላቸው፣ እንደ ልማዳቸውም መልካም ይሆንላቸው ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸልይ" (2007፣ ገጽ 67-68)። ይህ ንግግር እንኳን የሰዎችን ባህል ልናናንቅ፣ ልንጨቁን ይቅርና በማክበር እንደ ባህላቸው መልካም ይሆንላቸው ዘንድ እንድንጸልይ ይመክረናል። እንደዚህ ዓይነት ምክሮች በፍልስፍናው ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ህዝቦች ለዘመናት በተግባር ይታዩ የነበሩ ናቸው። ለምሳሌ በዘመነ መሣፍንት ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ተጓዥ ዳባዴ በዓይኑ ያየውንና በማስታወሻው ያሰፈረውን ከላይ አይተናል። ወልደ ሕይወትም እንደዚህ ዓይነቱን መከባበር ነበር ሲመክር የነበረው።

አንዱ ባንዱ ላይ መቀናናትና መታበይ ለመለያየትና ለመገዳደል እንዲሁም ለመበታተን የሚያደርሰው መከባበርና ብዝሃነትን ማስተናገድ ሳይቻል ሲቀር ነው። ይህም የሰዎች ስንፍና ነው። ይህን መሰሉን እኩይ ምግባር የአንጋረ ፈላስፋ ጸሐፊ (ተርጓሚ) እንዲህ ያስቀምጠዋል፤

> ሰዎች ስነፎች ቢሆኑ ነው እንጂ አይዋረዱም ነበር ቢበታተኑ ነው እንጂ አይሰንፉም ነበር። ቢለያዩ ነው እንጂ አይበታተኑም ነበር። ቢጣሉ ነው እንጂ አይለያዩም ነበር። እርስ

> በርሳቸው ቢቃኑ [ቢቀናኑ] ነው እንጂ አይጣሉም ነበር። እርስ በርሳቸው ቢተባበዩና አንዱ ባንዱ ላይ ቢኮራበት ነው እንጂ አቃኑም ነበር። እርስ በርሳቸው እየተዘባበቱ ነው እንጂ አይተባበዩም ነበር።
> ይህ ቃል የሰው የውርደቱ መጀመሪያ አንዱ ባንዱ ላይ መዘበት ሲሆን መጨረሻው ተበታትኖ መቅረት መሆኑን ይገልጻል" (፲፱፻፶፫፣ ገጽ ፻፴)።

የሰው ልጆች ሁሉ እኩል ናቸውና ልዩነታቸው ወደ መገዳደል ሳይሆን ወደ ጋራ ደህንነት እንዲያደርሳቸው መከባበርና አንዱ ያንዱን ባህልና ሃይማኖት፣ ባህልና እውቀት ይቀበል ዘንድ ግድ ይለዋል። ወልደ ሕይወትም "ነገር ግን ከእኔ ጋር ለማይተባበሩ ለእያንዳንዳቸው ሁሉ ሃይማኖታቸውን ይጠብቁ ዘንድ በፈቀዱትም ያምኑ ዘንድ መብት አላቸው" (2007፣ ገጽ 49) ማለቱ ለዚህ ነው። ምክንያቱም "ሰው ያለ ሌሎች ሰዎች እርዳታ ብቻውን ተወልዶና አድጎ ያገለግል ዘንድ አይችልምና" (ዝኒከማሁ፣ ገጽ 52)።

እንደ ወልደ ሕይወት የሰዎች አንድነት እና መተባበር የሚመነጨው ሁሉም በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩ የአንድ አባት ልጆች ናቸው ከሚለው ዲበአካላዊ ጥንተ ተፈጥሮና ለራስህ እንዲደረግብህ የማትፈቅደውን ለሌሎች አታድርግ በሚለው ግብረጋባዊ ኃላፊነት ነው። "ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ" የሚለውን መለኮታዊ ህግ ሲተነትነው "ባልንጀራ" ለዘመድ፣ ለወገን ወይም ለጓደኛ የሚሰጥ ሳይሆን ለሁሉም የሰው ልጆች የሚሰጥ እንደሆነ ይሞግታል (ዝኒከማሁ፣ ገጽ 64)።

ባጠቃላይ በኢትዮጵያ ፍልስፍናና የኢትዮጵያውያን ኑሮ ውስጥ ለብዝሃነት፣ ለሴቶች እኩልነትና ለአስተሳሰብ ልኅቀት ግብአት የሚሆኑ ሐሳቦችን ማግኘት እንደምንችል ከላይ ያለው ውይይት ያስረዳል። ይህ ብዝሃነት የሚያስተናግድና ሁሉን አሳታፊ ስልጡን ማኅበረሰብ በየእለት መስተጋብሩ ውስጥ በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ዘመን ተሻጋሪ ቁሳዊና መንፈሳዊ ልኅቀቶችን ያስመዘግባል። ይህም ዘላቂ ዕድገትን በትውልዶች መካከል ያለን በጎ ግንኙነት የሚያስቀጥል የትስስር ሰንሰለት ነው።

## ፯. ቀጣይነት ያለው ልዕልና

ቀጠይነት ያለው ዕድገት ማለት በተለምዶ ዘላቂ ልማት ወይም በእንግሊዝኛ "ሰስተይኔብል ዲቨሎፐመንት"[14] በመባል የሚታወቀው ነው። ሐረጉን በዚህ ጽሑፍ ውስጥ መንፈሳዊና ቁሳዊን ልዕልና፣ የሰው ልጆችን ከፍታ ለመግለጽ ተጠቅሜበታለሁ። ይህም በጾታ ወይም በባህል፣ በቋንቋ፣ በእድሜና በማንነት ልዩነት ሳያደርግ ትናንትን ከዛሬ የሚያስታርቅና ዛሬን ከነገ የሚያስተሳስር የልማት ቅብብሎሽ ጤናማነት የተረጋገጠበት ልማት ነው። ይህም በትውልዶች መካከል ያለን በጎ ተግባቦት የመንፈስ ትስስርና በባህሎች መካከል ያለን ጤናማ የዓላማ አንድነት የሚያረጋግጥ የአንድን ፖለቲካ ማኅበረሰብ እኩል የጸጋና የፍዳ፣ የመብትና የግዴታ ተካፋይነት የሚያረጋግጥ ነው። እንኳንም በሰዎች መካከል

[14] Sustainable Development

ይቅርና በሰውና በተፈጥሮ  መካከል ያለን ግቡዕ ግንኙነት የሚያቅፍ ሰፊ ትርጉም ያለው ነው። የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም ሪፖርት ቀጣይነት ያለውን ዕድገት እንዲህ ይተረጉመዋል።

> ቀጣይነት ያለው የሰው ዕድገት ማለት የኢኮኖሚ እድገት ብቻ የሚያስገኝ ሳይሆን የእድገትን ጸጋም በፍትሐዊነት የሚያከፋፍል፤ ተፈጥሮአዊ አካባቢን የሚንከባከብ እንጂ የማይበድል፤ ሰዎችን የሚያበረታታ እንጂ የማያገልል። ለጭቁኖችና ለድሃዎች ቅድሚያ የሚሰጥና ሰፊ ምርጫዎችንና መልካም አጋጣሚዎች ላይ ተሳታፊነታቸውን የሚያሰፋ ሕይወታቸውን በሚመለከቱ ውሳኔዎች ላይ ድምጻቸውን እንዲሰጡ የሚፈቅድ ዕድገት ነው። ለህዝቦች፣ ለአካባቢ፣ ለሴቶች የቆመ ዕድገት ነው።[15]

የሴቶች እኩልነት፣ ብዝሃነት እና ምክንያታዊ ማኅበረሰብ የሚያስፈልገውም ይህንን የማኅበረሰቡን ታሪካዊ ዳራና በጎ እሴቶችን የሚንከባከብና የነገን የጋራ እጣ ፈንታ የመወሰን አቅም ያለው ጠንካራ የመንፈስ ትስስር ያለው ዕድገት ባለቤት የሆነ ማኅበረሰብ ለመገንባት ነው። መሳይ ከበደ የኢትዮጵያን ዘመናዊነት ከጊዜ ጋር በማያያዝ ባተተበት መጣጥፍ የታሪክንና ያለፈን ትውፊት የዘነጋ እድገት ወይም ዘመናዊነት ውጤታማ ሊሆን እንደማይችል ነው (መሳይ ከበደ፣ 2009) ። እንደ መሳይ ከሆነ ለኢትዮጵያውያን ጊዜ አላፊ ሳይሆን ተተኪና ራሱን የሚደግም የመፈራረቅ የድግግሞሽ ሂደት ነው። ይህ የተፈራራቂነት የጊዜ እሳቤም ስለ ዕድገት እና ዘመናዊነት አንድ ቋሚ ነገርን ብቻ እንዳንከተል (የአውሮፓን አርአያነት) በራሱ በኢትዮጵያውያን የጊዜ እሳቤ ራሱን የቻለ የስልጣኔ መንገድ እንድንከተል ጥቆማ ያደርጋል የሚል ነው። ይህም ህሉፍን እንደ ኋላ ቀር አድርጎ ከመፈረጅ የሚታደግ ይሆናል ማለት ነው (መሳይ፣ 2009)።

ፈቃደ አዘዘም ሰውና ሰውነት ያለፈ፣ ያሁንና የሚቀጥለውም ትውልድ መጠሪያ የወል ስም እንደሆነ ይሞግታል። “ሰው ከመጸነሱ በፊት፥ [በልደት ቀኑ፥] በሕይወት ዘመኑ፥ በሞቱ ጊዜና ከሞቱም በኋላ የተከናወኑ ቁሳዊና መንፈሳዊ ባህላዊ ሥርዓቶችና ድርጊቶች የሚጠሩበት የጥቅል ስም ነው ማለት የሚቻል ከመሰለኝ ቆይቷል” (2004፣ 99)።

በዚህ ጉዳይ ሰፊ ምርምር የሚያስፈልገው ቢሆንም ይህንን የትውልዶችን መወራረስ እና ቀጣይነት ያለው ስልጣኔ ቅብብል ዘርዓ ያዕቆብ በሐተታው አልዘነጋውም። የታሪክ

---

15 “Sustainable human development is development that not only generates economic growth but distributes its benefits equitably; that generates [sic] the environment rather than destroying it; that empowers people rather than marginalising them. It is development that gives priority to the poor, enlarging their choices and opportunities and providing for their participation in decisions that affect their lives. It is development that is pro-people, pro-nature, projobs and pro-women” (Quoted in Workineh, 2011, p. 6).

እና የስልጣኔ ቅብብል እንደሚያስፈልግ ከአደራም ጭምር ለደቀ መዝሙሩ እንዲህ ይለዋል፤

> ከእኔ በኋላ የሚመጡት እንዲያውቁኝ ግን ይህንን እስከ ሞቴ ድረስ በእኔ ዘንድ ተደብቆ የኖረውን እጽፍ ዘንድ ወደድሁ። ከሞትሁ በኋላ አስተዋይና ተመራማሪ ሰው ቢገኝ ከእኔ ሐሳብ ላይ ሐሳቡን ይጨምርበት ዘንድ እለምነዋለሁ።… የሀገራችን ሰዎች በእግዚአብሔር ረድኤት ጥበበኞች እንዲሆኑና እውነትንም ወደማወቅ እንዲደርሱ እኔ የጀመርሁትን አንተ ፈጽመው። ሐሰትን እንዳያምኑ፣ ዐመጻንም ተስፋ እንዳያደርጉ ከከንቱ ወደ ከንቱ ፈጽመው እንዳይሄዱ እውነትን ይወቁ እንጂ ወንድሞቻቸውንም ይውደዱ። እስከ ዛሬ ድረስ እንዳደረጉት፣ ከንቱ በሆነው ሃይማኖታቸው ከእንግዲህ ወዲህ አይጠሉ (2007፣ 35)።

ለስልጣኔ ቅብብል የአስተሳሰብና የምርምርን ትልቅ ፋይዳ ሲያጎላ የጠቀስነው አንቀጽ በልዩቶች መካከል የሚነሳን ጥላቻ እንዲያስወግዱም ይመክራል። የፈላስፋው ሃሳብ ካልተለመደው የኢትዮጵያውያን ሃይማኖታዊ ድርሳናት አጻጻፍ ወጣ ብሎ ከኔ የጎደለውን አንተ ጨምርበት አለን እንጅ "ዘሰረቀ ወዘፈሐቀ ለይኩን ውጉዘ" አላለም። ባለ አደራው ወልደ ሕይወትም ይህንን የሥልጣኔ ቅብብሎሽ አጽንኦት ሰጥቶ እንዲህ ይላል። "እኔም ምትኩ የምባለው ወልደ ሕይወት ከዚህ በኋላ እርሱ የሰራውን መልካም ነገር ተኳላው ታውቁ ዘንድ በመምህሬ መጽሐፍ ላይ ይህችን ትንሽ ነገር ጨመርሁ። እግዚአብሔር በገለጸልኝና ዘርዓ ያዕቆብ ሃምሳ ዘጠኝ ዓመት ባስተማረኝ መሠረት ለኢትዮጵያ ልጆች እውቀትና ተግሣጽ እንዲሆን እኔም እነሆ ሌላ መጽሐፍ ጻፍሑ" (ዝኒከማሁ፣ ገጽ 37)። ከመምህሩ ከተማረውና በሕይወት ዘመኑ ከተመራመረው የእውቀት ጸጋ በመጽሐፉ ካስቀመጠ በኋላ በመዝጊያው ምዕራፍ፣ በመምህሩ አርአያነት፣ ለመጭው ትውልድ የሥልጣኔን ቅብብሎሽ የቤት ሥራ በውብ ቃላቱ እንዲህ ያሳስባል፤

> በእግዚአብሔር ረድኤት ይህንን በጥቂቱ እነሆ ጻፍሁ። ይህችን መጽሐፍ የምታነብ ወንድሜ ሆይ አንተም ጥበብ ካለህ እግዚአብሔር የገለጸልህን ጻፍ። ከእንቅብ በታች እንዳስቀመጧት መብራት አትሁን። በምድራችን ላይ ጥበብ እንዲበዛ ኃጢአተኛና እውነት ማድረግን የማያውቅ ፈጽሞ እንዲጠፋ፤ ለሃገራችን ልጆች እውቀትና ተግሣጽ እንዲሆን፤ የጥበብህን ብርሃን አውጣው እንጂ። ልዑል የሆነው የፈጣሪያችንን ሥልጣን አላወቁምና። አውቀውስ ቢሆን ኖሮ ከንቱ በመከተላቸው ባፈሩ ነበር። በዘመናችን ሰነፎች የሆኑ ወገኖቻችንን ቅንዓት ይዟቸዋልና። ስለ ሃይማኖታቸው ሥርዓት ተገዳደሉ። የፈጣሪያቸውንም ሥርዓት አላወቁም (ዝኒከማሁ፣ ገጽ 105)።

እነዚህ ቃላት ለውይይታችን ማሠሪያ ናቸው። ባንድ በኩል በትውልዶች መካከል ሊደረግ የሚገባው ጤናማ የታሪክና ሥልጣኔ ቅብብሎሽ ይጠቁማሉ። በሌላ በኩል ጥበብ በምድራችን ታብብ ዘንድ የዘመኑ ትውልዶች የሚጠበቅባቸው ሚና ምን እንደሆነ ያሳያል። ይህም ብቻ ሳይሆን ሰዎች ሰው ሰራሽ በሆኑ ልዩነቶቻቸው (በተለይ ከእግዜር የመጣች

ናት በሚሏት ሃይማኖት) መገዳደላቸው ምን ያክል ጥበብ የጎደላቸው መሆናቸውን በግሳጼ መልኩ ያስቀምጣል። ከ300 ዓመታት በፊት ብዝሃነትን፣ ሥልጣኔንና አብሮነትን በጠቢቡ አንደበት ተቀምመው በተጻፉ ቃላቶቹ አማካኝነት ያገኘናቸው ዘመን አይሽሬ የፍልስፍና ጸጋዎች መገለጫዎች ናቸው።

## ፯. ማጠቃለያ

ያነሳነው ርእስ ሰፊ ጉዳይ ነው። ከላይ በሰፊው እንዳየነው ሥልጣኔ ሁሉን አሳታፊ መሆን አለበት። ይህ የሚሆነው ደግሞ ልዩነት በሰለጠነ መንገድ ሲያዝ ነው። ስልጣኔና ምርምር የሰው ልጆች ጸጋዎች ናቸው። ከዚህ በተቃራኒ መሆን ደግሞ ከለባዊት ነፍስ ጋር የማይስማማ ኃጢአትም ነው። በዘመን ተሻጋሪ የኢትዮጵያ ፍልስፍናዎች ውስጥ ለሴቶች እኩልነት፣ ለብዝሃነት፣ አስተሳሰብ ስልጣኔና ቀጣይነት ላለው ዕድገት ግብአት የሚሆኑ ሃሳቦችን በሥፋት እንደምናገኝ ከላይ አይተናል።

የዘመናችን የእድገት፣ የፌደራሊዝምና የትምህርት ስርዓቶችና ፖሊሲዎች ልብ ሊሉት የሚገባው ትልቁ ነገር ቢሆን በዘመን ሂደት ውስጥ ኢትዮጵያውያን ያቆዩልንን ሃገር በቀል እውቀት በደንብ መንከባከብና ወደ ተግባራዊ ፋይዳዎች መለወጥ ይገባናል። ይህ ያልሆነ እንደሆነ ግን ከወላጆቹ የተነጠለ፣ ከዘመኑ የተገለለ፣ ከማንነቱ የተፋታ ትውልድ እንፈጥራለን። ባህሉን የዘነጋ ትውልድ ደግሞ እንኳንም ዘላቂ ልማት ይቅርና ለዛሬውም ኑሮ የሚሆነውን የሕይወት ትርጉም ማጣጣም አይቻለውም። ባህል ደግሞ ማንነትን ሰብስቦ የያዘ የትናንትና የዛሬ እሴቶች ውህድ ነው።

ትክክለኛ ልማት በትውልዶች መካከል የመንፈስ ትስስርና በባህሎች መካከል የዓላማ ቁርኝት ማምጣት የሚችል መሆን አለበት። ለዚህ የአስተሳሰቦችና የባህሎች ተግባቦት ደግሞ ፍልስፍና ትልቅ ሚና አለው። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያውያን ዘመን ተሻጋሪ ፍልስፍና ከዘመናዊ ሳይንስና የአውሮፓ ፍልስፍና ጋር በማዋሃድ ዘመን ተሻጋዊ የሰው ልጆች ዕድገት ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

በተለይ የዘመናችን መካነ አእምሮዎች ይህንን ሥራ ከመወጣት አንጻር ትልቁን ድርሻ ይወስዳሉ። በተቋቋሙበት አካባቢ የሚገኘውን ማኅበረሰብ ሀገር በቀል እውቀት ፈልፍለው በማውጣት መልካም ቁሳዊና መንፈሳዊ ውርሶችን ላሁኑ ትውልድ በሚመጥን መልኩ ሊተገብሩት ይገባል (እጓለ ገብረዮሐንስ፣ 2003)። ይህ ካልሆነ ለይስሙላ የሚመስል አብለጭላጭ ቁሳዊ ሥልጣኔና በወፍ ዘራሽ ባህል የተቀየጠ የኑሮ ዘይቤ አካላዊና ስነ ልቡናዊ ልምሾነትን ያስከትላል።

ፖሊሲ አውጭዎች፣ የፖለቲካ መሪዎች፣ የህዝብ መብት ተቆርቋሪዎች ሁሉም ማኅበረሰብ የወላጆችን፣ ትውፊታዊ ጠቢባንን[16]፣ የሃይማኖት መሪዎችንና የልሂቃኖችን ይሁንታ የሚያካትት የልማት እቅድ ሊያወጡና ሊተገብሩ ይገባል።

---

[16] Sages

## ዋቢ መጻሕፍት

### ሀ. አማርኛና የግዕዝ ምንጮች

መሳይ ከበደ። "የኢትዮጵያ ግዜ ግንዛቤና ዘመናዊነት።" (ተርጓሚ ቤተልሄም ሃይሉ ደጀኔ) ጋይተን ዩኒቨርሲቲ፣ (2009)።

ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ (ሊቀ መዘምራን)። (ተርጓሚ) "አንጋረ ፈላስፋ (የፈላስፎች አነጋገር)።" (፲፱፻፶፫)።

ተክለ ጻዲቅ መኩሪያ። "የኢትዮጵያ ታሪክ: ኑብያ-አክሱም ዛጉዬ እስከ አጼ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት" ፩ኛ መጽሐፍ። ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ (፲፱፻፶፮)።

አለቃ ያሬድ ፈንታ ወልደ ዮሐንስ። (ተርጓሚ) "ሐተታ ዘርዓ ያዕቆብ ወሐተታ ወልደ ሕይወት:- የኢትዮጵያ ፍልስፍና"፣ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ.የተ. የግ.ማ. አዲስ አበባ፣ (2007)።

ኢያሱ በሬንቶ። "ተግባራዊ ፍልስፍና (Practical Philosophy) በ17ኛው ክፍለ ዘመን (ከ.ዘ) ኢትዮጵያ:- ሐተታ ወልደ ሕይወት እንፍራንዛዊ" በአባይ የባህል ማዕከል 3ኛው አገር አቀፍ ኮንፈረንስ 2009 ዓ.ም የቀረበ፣ ዐውደ ጥናት መድብል ላይ የታተመ፤ ገጽ 93-136፣ (2010)።

እጓለ ገብረ ዮሐንስ። "የከፍተኛ ትምህርት ዘይቤ።" 2ኛ እትም፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፣ (2003)።

ገብረሕይወት ባይከዳኝ (ነጋድረስ)። "መንግሥትና የህዝብ አስተዳደር፤ በየነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ ሥራዎች ውስጥ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፐረስ፣ አዲስ አበባ፣ (2002)።

ገነት አየለ አንበሴ (ተርጓሚ)። "አርኖ-ሚሼል ዳባዲ: በኢትዮጵያ ከፍተኛ ተራሮች ቆይታዬ።" ክፍል 1፣ (2009 E.C) ።

ፈቃደ አዘዘ። "ቁዘማ:- ፎክሎር (ባህል) እና ልማት በኢትዮጵያ" in ባህልና ልማት በኢትዮጵያ ሽፈራው በቀለ (2004 ዓ.ም) (አርታኢ) ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ፣ አዲስ አበባ፤ ገጾች 97-138፣ (2004)።

### ለ. በእንግሊዝኛ የተጻፉ ምንጮች

Greenfield, R. "Ethiopia: A New Political History." (2013 Addis Ababa reprint), Pall Mail Press Ltd, London, (1965).

Huntington, S. P. "The Clash of Civilizations?" In Foreign Affairs *Volume 72 No.3 pp. 22-49,* 1993).

Levine, D. N. "Greater Ethiopia: The Evolution of a Multiethnic Society", The Univertiy of Chicago Press, Chicago & London, (1974).

Sumner, C. "Classical Ethiopian Philosophy." Comercial Printing Press, Addis Ababa, (1985).

Tim LeBon, "What is Practical Philosophy?" Aceessed at http://www.timlebon.com/blog/2007/01/what-is-practical-philosophy-number-2.html (2007).

Workineh Kelbessa "Indigenous and Modern Environmental Ethics: A Study of the Indigenous Oromo Environmental Ethic and Modern Issues of Environment and Development". The Council for Research in Values and Philosophy, (2011).

*Eyasu Berento Assefa,*
*Faculty of Social Sciences*
*Kotebe Education University*
*(formerly known as Kotebe Metropolitan University)*